የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች
# የዲስፕሊን መመሪያ

(መመሪያ ቁጥር፡ ሳከትሚ/002/2012)

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
መስከረም 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ክፍል ሁለት
## መብቶችና ግዴታዎች

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 በአንቀጽ 38ና 39 የተዘረዘሩትን እንዳሉ ሆነው በተጨማሪ የተማሪዎች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ክፍል ቀርበዋል።

**አንቀጽ 5፡- የተማሪዎች መብቶች፣**

1. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሴኔት ባወጣው የትምህርት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በነጻነት የመማር፣ የመጠየቅ፣ የመመራመር፣ የመረዳዳት፣ የማወቅ፣ ሳይንሳዊና ጥበባዊ ክህሎትን የማሳደግ፣ ልቆ መገኘት፣
2. በመማሪያ ክፍል፣ በዩኒቨርሲቲ ግቢና በህብረተሰቡ ውስጥ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፣
3. በዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ህገ-መንግስታዊና ሰብዓዊ መብታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ የመኖር፣
4. በዩኒቨርሲቲ ጉዳዮች ላይ በህጋዊና በሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነጻነት የማራመድ፤
5. ማንኛውንም አይነት አድሎ ወይም ትንኮሳ እንዳይደርስባቸው ህጋዊ ከለላን የማግኘት፤
6. በማንኛውም የመምህርና የተማሪ ግንኙነት የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፤
7. ስለአካዳሚያዊ ብቃታቸው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፣ ኢ-ፍትኃዊ ምዘና ሲፈጸም ቅሬታን በዩኒቨርሲቲው ስርዓት መሠረት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትሕን የማግኘት፤
8. ግልጽነት ባለው ስርዓት መሠረት የመምህራንንና ሌሎች አካዳሚክ ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም መሙላትና የአፈጻጸም ግምገማው ላይ በመሳተፍ አስተያየት የመስጠት፣
9. በትምህርት ማህደራቸው ዉስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች በሚስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለጹበት ሁኔታ የሚወስን አስማማኝ ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፣
10. የተማሪው የጋራ ጥቅሞችን በህጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ህጎች በተቋቋመና የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች በሙሉ በአባልነት በሚያቅፈው የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ህብረት አባል የመሆን፣
11. በዩኒቨርሲቲው ደንብና ስርዓት መሠረት በግልም ሆነ በማህበራቸዉ አማካይነት በዩኒቨርሲቲው መገልገያዎች የመጠቀም፤
12. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ድንጋጌዎችና የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በማህበራቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው አካደምያዊና አስተዳደራዊ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፤
13. የፈተና ውጤትን በወቅቱ የማየት፣ ቅሬታ ካለ የማቅረብ
14. የፈተና ውጤት /Grade Report/ በወቅቱ የመቀበልና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በማቅረብ አግባብነት ያለው የትምህርት ማስረጃ በጊዜ የማግኘት፣
15. የየሴሚስተሩን የመጨረሻ የፈተና ፕሮግራም በቂ በሆነ ጊዜ (ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት) የማወቅ፣
16. ማንኛውም መደበኛ ተማሪ የወጭ መጋራት ውል ከፈረመ ወይም ለአገልግሎቱ የሚገባውን ክፍያ በቅድሚያ እስከ ፈፀመ ድረስ ዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውን የምግብ፣ የመኝታ፣ የህክምናና የመዝናኛ አገልግሎቶችን የማግኘት፣
17. ከትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ሀሳቦች የማቅረብ፣ የመከራከርና የመወያየት፣